ዴሞክራሲያ
* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 42 ቁ. 4

ጥር/ የካቲት 2009 ዓ.ም

# ሕዝባዊ ዐመጽና የሥርዓት ለውጥ

የአገራችን የቅርብ ታሪክ በየካቲት ወር ውስጥ አስደሳችም አሳዛኝም ሁኔታዎች እንደተፈጸሙ ይነግረናል። በየካቲት ወር የኢትዮጵያ ነጻነትና ሉዓላዊነትን ያረጋገጡ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያኮሩ፤ ለሙብቱ ለእድገቱና ለብልጽግናው የተሰፉ ጭላንጭል ያሳዩ ክስተቶች የተፈጸሙ እንደመሆናቸው ሁሉ በርካታ ኢትዮጵያውያን የተጨፈጨፉበትና መስዋዕት የሆኑበት፤ ከፋፋዩና አምባገነኑ ዘረኛ ቡድን ውልደት ያገኘበት አሳዛኝ ወር እንደነበርም ተገንዝበናል። በየካቲት 23 1888 ዓ.ም የተከናውነውን የዓድዋ የድል በዓል እና በየካቲት 66 የአዔውን አፋኝ አገዛዝ የገረሰሰውን የ1966-ኡን የለውጥ እንቅስቃሴ በደስታና በሆታ ስናከብር በየካቲት 12 በአዲስ አበባ በግራዚያኒ ፋሽስቶች በግፍ የተጨፈጨፉትን ወይንም ዘረኛውና ጨፍጫፊው የወያኔ ቡድን ነፍስ የዘራበትንና ህልውና ያገኘበትን ክስተት በሀዘን እናስባለን።

በዘመናዊ መሳሪያ ራሱን አስታጥቆና ጦሩን በሚገባ አሰልጥኖና አደራጅቶ በርካታ ባንዳዎችንና ሹምባሾችን አሰባስቦ አገራችንን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ወረራ ያካሄደውን የጣሊያን ጦር ድባቅ በመምታት አባቶቻችን የተጎናጸፉት የአድዋ ድል በርግጥም እኛ ኢትዮጵያውያንን በዓለም አቀፍ ደረጃ እንድንከበር ያደረገ፤ ኢትዮጵያውያንን ሁሉ ያኮራ፤ የአገር አፍቃሪነታችን፤ የጅግንነታችንና የአንድነታችን መገለጫ የሆነ ታላቅ ክስተት ነው። ይህ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለመላው ጥቁር ሕዝብ ኩራት አርዓያና የትግል መመሪያ የሆነው የአድዋው ድል በየአመቱ በደስታና በኩራት እየተከበረ ለተከታታይ ትውልድ መተላለፍ ይኖርበታል።

በአሁኑ ወቅት አገራችንና ሕዝባችን ለሚገኙበት አሳዛኝ ሁኔታ ትምህርትና ግንዛቤ፤ ተስፋና ራዕይ ሊሰጥ የሚችለውና ኢትዮጵያዊያን ሁሉ በአንክሮ ሊያስታውሱት የሚገባው ሌላው ክስተት ደግሞ የየካቲት 66-ኡ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ነው። የዐፄውን ሥርዓት ያናጋውና በኋላም እንዲገረሰስ ያደረገው የየካቲቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የረጅም ጊዜ የሕዝብና የተራማጅ ኃይል ትግል ውጤት ነበር። ቀደም ብሎ ተማሪውና ተራማጅ ኃይሉ መሬት ለአራሹ ይሰጥ፤ የብሔርና የብሔረሰብ እኩልነት ይስፈን፤ የሃይማኖት እኩልነት እውን ይሁን፤ የባላባታዊ መንግሥት ይወገድ በማለትና ሌሎችንም መሪ ሀሳቦች በማንሳት ለረጅም ዓመታት ሲያካሂዱት የነበረው ተጋድሎ በሂደት ወደ ኅብረተሰቡ ዘልቆ በየካቲት 66 መምህራን፤ ሠራተኞች፣ ወታደሮች፣ ነጋዴዎች፣ ተማሪዎች፣ የመንግሥት ሠራተኞች፣ ሴቶች ወንዶች፣ የተለያዩ የእምነት ተከታዮች፣ ...ወዘተ የኅብረተሰቡን ብሶት በማንሳት በእንቅስቃሴው ተሳትፈዋል፤ ገኸውን ክፍል ታግለዋል። የትግል መፈክሮችና ጥያቄዎችም አካባቢያዊ ከሆኑ ግላዊ ጥያቄዎች ውጭ ሰፍተው ወደ አገራዊና ሕዝባዊ እንዲሁም ወደ ሥልጣንና የሥርዓት ለውጥ ጥያቄዎች ተሸጋግረዋል። በእንቅስቃሴው መጀመሪያ ወቅት የደሞዝ ጭማሪንና የኑሮ ሁኔታን መሻሻል ያነገበው የወታደሩ

ጥያቄ፤ የነዳጅ ዋጋ መቀነስን ዓላማ አድርጎ የነበረው የታክሲ ነጅዎች አድማ፤ የትምህርት አሰጣጥ መስተካከልንና የደሞዝ ጭማሪን ያስተጋባው የመምህራን ጥያቄ፤ የሃይማኖት እኩልነትንን ግምባር ቀደም በማደረግ የተደረገው የምዕመናን እንቅስቃሴ፤ አርሶ አደሮችና ሌሎች ተራማጅ ኃይሎች ሲያቀነቅኑት የነበረው የመሬት ላራሹ ጥያቄ እንዲሁም ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ያቀረቧቸው ጥያቄዎች በትግሉ ሂደት ዓይነትና ጥራት እያገኙ ሄደው አጠቃላይ ወደ ሆኑ የመብትና የሥርዓት ለውጥ ጥያቄዎች ተለውጠዋል። የመናገር የመደራጀት የመሰብሰብ ነፃነቶች ይከበሩ፤ ዴሞክራሲያዊ መብቶች እውን ይሁኑ፤ የዐፄው ሥርዓት ተወግዶ ሕዝባዊ መንግሥት ይመሥረት የሚሉትና ሌሎች መሠረታዊ የሆኑ ጥያቄዎች ጎላ ብለው ወጥተዋል። መሠረታዊ የሆኑት ጥያቄዎቻቸው ሊፈቱ የሚችሉት ጨቋኙ ሥርዓት ተወግዶ በምትኩ በሕዝብ የሚቋቋም፤ ለሕዝብ የሚያገለግልና በሕዝብ ቁጥጥር ስር የሚውል ሥርዓት ሲመሠረት መሆኑን አውቀው ዜጎች ለሕዝባዊ መንግሥት ታግለዋል።

በሕዝብ ትግልና ግፊት የዐፄው አገዛዝ በመጨረሻ ሊገረሰስ ቢችልም በጊዜው የተደራጀውና የአገሪቱን የመከላከያ ኃይል ይቆጣጠር የነበረው የምርጥ መኮንኖቹ ወታደራዊ ደርግ የሕዝብን እንቅስቃሴ አግቶ፤ የሕዝብን መብት አፍኖ፤ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት የሚለውን ሕዝባዊ ጥያቄ በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ለውጦ ሥልጣኑን ለመቆጣጠር በቅቷል። ፈላጭ ቆራጩ የደርግ አገዛዝ በአስራ ሰባት ዓመት የሥልጣን እድሜው የሕዝቡን መብት ሙሉ በሙሉ አፍኖ የግድያና የጭፍጨፋ አገዛዙን አስፍኖ ሰፊውን ሕዝብ እያሰቃየ ቢዘልቅም፤ በልዩ ልዩ የፖለቲካ ኃይሎች ከተለያዩ አቅጣጫዎች በሚደርስበት በትር እየተገዘገዘና የሕዝብን ተቀባይነት ሳያገኝ ሥልጣኑን ሳያደላድል ዘልቋል። በመጨረሻም የተከማቸውን የሕዝብ ብሶትና እሮሮ ተንተርሰው ሲንቀሳቀሱ የነበሩት ጠባብ ቡድኖች በውጭ ኃይሎች ተጠናክረው በሰነዘሩት ጥቃት ከሥልጣን ሊወገድ ችሏል።

ጨካኙን የደርግ አገዛዝ ያስወገደው ዘረኛና ጠባብ ቡድን በስልትና በዘዴ ሥልጣኑን ተቆጣጥሮና አጠናክሮ የሕዝቡን የሥልጣን ጥያቄ ወደ ጎን አድርጎ፣ ተከታታይ አገዛዞች በሕዝቡ ላይ ሲያካሄዱት የነበረውን ጭቆናና በደል በስፋትና በጥልቀት ቀጥሎ ሕዝብን በማሰቃየት ላይ ይገኛል። ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የወያኔ አገዛዝ በሕዝብ ላይ ያካሄደውን ግፍና መከራ ሆነ የዘረጋውን የአስከፊ የአገዛዝ ሥርዓት እዚህ ላይ በዝርዝር ማቅረብ አስፈላጊ ባይሆንም ካለፉት አገዛዞች የከፋና የበረታ፤ የአገሪቱን ህልውና አደጋ ላይ ያስቀመጠ የጥፋት መልክተኛ የሆነ አገዛዝ ነው ብሎ መደምደም ይቻላል። የወያኔ አገዛዝ ገና ሥልጣን ሲይዝ ለአንድ የጎሳ ቡድን የበላይነትና ተቆጣጣሪነት አመች የሆነ ሕገ-መንግሥት ነድፎና አገሪቱን በጎሳ ክልሎች ከፋፍሎ የፖለቲካ ሥልጣኑን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሯል። የወታደሩን፣ የጸጥታውን፣ የአስተዳደሩንና የፍርዱን ተቋም እንዲሁም ዋና ዋና የኢኮኖሚ መስኮችን ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር የፈላጭ ቆራጭ አገዛዙን ያሰፈነ ሲሆን የብዝበዛ አውታሮችንም አስፋፍቷል። ከአንድ ብሔር የተውጣጡ ገዥዎችና የጥቅም ተካፋይ የሆኑ ተባባሪ ባለሥልጣኖች የበላይ የሆኑበት ሌላው ደግሞ እንደሁለተኛ ዜጋ የሚታይበት የፖለቲካ ሥርዓት መሥርቷል። የሕዝብ መሠረታዊ ዴሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች ታፍነዋል፤ መብቱን የጠየቀውና ተቃውሞ ያሰማው ዜጋ ይታሰራል፣ ይቀጠቀጣል፣ ይገደላል። የአምባገነን ሥልጣን እንጅ የሕግ የበላይነት የለም፤ ፍትህ ከናካቴው ጠፍቷል፤ የደኻው መሬት ተቀምቶ ለውጭ ባለሀብቶች ተቸብችቧል፤ የአገር ሀብት ተዘርፎ ወደ ወደ ውጭ ተግዟል፤ ሥራ አጥነት ተስፋፍቷል፤ ረሃብ ያለማቋረጥ በሀገሪቷ ነግሷል፤ በአፈና አገዛዝ በኢኮኖሚ ችግር ዜጎች ወደ ወደውጭ ተሰደዋል፤ ... ወዘተ... ወዘተ...።

ካለፈው ዓመት መባቻ ጀምሮ በተከታታይ በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ሲካሄዱ የነበሩት ሕዝባዊ አመጾችና የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በወያኔ የሃያ አምስት ዓመት የግፍ አገዛዝ አንጀቱ ያረረው ሕዝብ ብሶት የወለዳቸው ናቸው። ቀደም ባሉት

ዓመታት በክርስቲያን አባቶች በኋላም በሙስሊሙ ኅብረተሰብ የተደረጉት እልህ አስጨራሽ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን ተከትለው ለአንድ ዓመት ከሶስት ወር ለሆነ ጊዜ በደቡብና በሰሜን፣ በምሥራቅና በምዕራብ ኢትዮጵያ የተካሄዱት ሕዝባዊ እንቅስቃሴዎች እንደየካቲት 66-ኡ እንቅስቃሴ መነሻ ምክንያታቸው ውሱንና አካባቢን መሠረት ያደረጉ ቢሆኑም በሂደት ስፋትና ጥራት እያገኙና እያደጉ ሄደው ወደ ሥርዓት ለውጥ ጥያቄዎች ተለውጠዋል። በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ስም ሊካሄድ የነበረውን ዐይን ያወጣ የመሬት ዝርፊያ በመቃወምና እንዲሁም ከወልቃይት የማንነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ አገዛዙ ያካሄደውን የአፈና እርምጃ በመቃወም በኦሮሞውና በአማራው አካባቢዎች የተጀመሩ እንቅስቃሴዎች ትግሉ እያደገና እየጎመራ ሲሄድ "አምባገነን አገዛዝ ይወገድ፤ ሕዝባዊ መንግሥት ይመሥረት" በሚሉ ጥያቄዎች ተተክተዋል። ሌሎች አካባቢዎችም ስፋትና መጠናቸው ይነስ እንጅ ተመሳሳይ ሕዝባዊ ጥያቄዎችን አንግበው አገዛዙን ወጥረዋል።

ላለፉት 25 ዓመታት አገዛዙ በተለያዩ ስልቶች በኅብረተሰቡ ላይ የጫናቸውን የጎሳ፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋና የክልል፣ ...ወዘተ ልዩነቶችን ሰብረው በሕዝብ መካከል አንድነትን፣ መተሳሰርን፣ መደጋገፍን፣ አጠናክረው በመቀጠል ላይ የነበሩት ሕዝባዊ አመጾች እንደየካቲት 66-ኡ እንቅስቃሴ የአገዛዝ ሥርዓቱን ሊገረስሱ ባይችሉም ባገዛዙ የሥልጣን ዕድሜ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ገዥውን ክፍል ከመሠረቱ ያናጉ መሆናቸው አይካድም። የገዥውን መደብ የክፍፍል ተንኮል የሰበሩ፤ ሆዳሙንና ለጥቅም ያደረውን ያስከዱ፤ በሥልጣን ላይ ያሉትን የገዥውን ክፍል አባላት እርስ በርስ ያተራመሱ እንቅስቃሴዎች ነበሩ።

አገዛዙ በሕዝባዊ አመጹ ጥንካሬና ስፋት ከመደናገጡ የተነሳ ህይወቱን ለማቆየት የተለያዩ እርምጃዎችን ወስዷል። በአይምሮ የማሰብ፤ በመንፈስ የመመኘት እንዲሁም የመናገር ሆነ የመስማት፤ እጅን የማንቀሳቀስ ሆነ በእግር የመራመድ መብት የሚከለክለውን አፋኝ የሆነውን የአስቸኳይ ጊዜ አውጀ እንቅስቃሴውን ለማስቆም ሞክሯል። የወያኔው አፋኝ አዋጅ ዜጎች እንዳይናገሩ እንዳይሰበሰቡ፤ የተቃዋሚ ዜና ማሰራጫዎችን እንዳያዳምጡ፤ የተቃዋሚ ጽሁፎችን እንዳያነቡ፤ እጃቸውን አጣምረው ተቃውሟቸውን እንዳይገልጹ፣ ተቃዋሚ ናቸው ተብለው ከተመደቡት ወይም ከሚጠረጠሩት ጋር እንዳይገናኙ እንዳይነጋገሩ ይከለክላል። በደርግ ጊዜ ያሰበና ያሳሰበን የሚቀጣ አዋጅ ታውጆ የሁሉም መሳለቂያ ሆኖ እንደነበር የሚታወቅ ሲሆን የወያኔም ዓይን ያወጣ አዋጅ ከትዝብትና ከስላቅ ያመለጠ አልሆነም። በአስቸኳይ አዋጁ ስም በርካታ ወገኖች ተገድለዋል። በአንዳንዶች ግምት ከ40 ሺህ በላይ የሆኑ ዜጎች በየማጎሪያ ሰፈሮች ውስጥ ታስረው በልዩ ልዩ የጭካኔ ተግባሮች ተሰቃይተዋል፤ ንብረቶቻቸው ተዝርፈዋል። የአዋጁ የመጀመሪያው ዓላማ በወታደራዊ አገዛዝ የፍርሃት ድባብን አስፍኖ የሥልጣን ዕድሜውን ማራዘም ስለነበር፤ አገዛዙ ከአመጹ ጥቂት ፋታ በማግኘቱ አዋጁ ግቡን መቷል በማለት እየተኩራራ ይገኛል።

አገዛዙ ከኃይል እርምጃው ጎን ለጎን አስመሳይ እርምጃዎችንም ወስዷል፤ ቲያትሩና ድራማውን በየመስኩና በየደረጃው አሳይቷል። በአዋጅ ስብሰባ እንዳያደርግ የተከለከለ ዜጋ በግድ ለስብሰባ ተጠርቷል፤ በአዋጅ አፉ እንዳይናገር የተለጎመው ወገን ወያኔ በጠራው ስብሰባ ላይ ስለባለስልጣኖች ድክመት፤ ስለአስተዳደር ጉድለት የመሰለህን ተናገር ተብሎ ተጠይቋል። አንጀቱ ያረረው ሕዝብ ከወያኔ በላይ ብልጥ ሆኖ የልቡን በልቡ ይዞ እየሳቀና እየሸነገለ ሸኝቶታል። በወያኔ ድርጅትና በተለጣፊ ድርጅቶች ውስጥም በጥልቅ መታደስ በሚል ፈሊጥ ግምገማ ሲያካሂድ ቆይቷል። የወያኔ ቁልፍና ነባር ተጋዳላዮችን የማይነካ የበታቾችንና ተለጣፊዎችን ሽንቆጥ የሚያረጉ እርምጃዎች ተወስደዋል ተብሏል። አጥፈተዋል የተባሉት ከሹመታቸው ተነስተው በአዲሶች ሲተኩ፤ ወደ ሌላ ቦታ ሲዛወሩና ከሥራ ሲባረሩ ሌሎች ደግሞ ሲታሰሩና ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ታይተዋል። ሥራ አጥ ወጣቶችን ሥራ ለማስያዝ በጀት ተመድቧል ተብሏል። በዩኒቨርስቲ የተመረቁት

ወጣቶች በእንጨት ሥራ ላይ በመሰማራታቸው ወይም የኮብል ስቶን ግምበኛ መሆናቸው ትልቅ እመርታ ተብሎ ተደስኩሮለታል። አልፎ ተርፎም አሸንቀጥሮ ጥሏቸው የነበሩትና ሕጋዊ ከተባሉት የተቃዋሚ የፖሊቲካ ድርጅቶች ጋር ድርድርና ውይይት እየተደረገ ነው በማለት መመጻደቁን ተያይዞታል። የተቃዋሚ ድርጅቶችን መሪዎች አስሮ እያሰቃየ፤ ሰርጎ በመግባትና በመከፋፈል ህልውናቸውን አዳክሞ እያመነመነና ቢሮዎቻቸውን እየመዘበረ ባለበት ሁኔታ ውይይትና ድርድር የሚለው ለለበጣ መሆኑን አዕምሮው የተዘጋ ደንቆሮ እንኳ አይስተውም። ገባ ብሎ ውስጡ ሲመረመር ደግሞ ከሚሰበሰቡት ውስጥ ሶስት አራተኛው የሚሆኑት አገዛዙ ጠፍጥፎ የሠራቸው፣ በሚያስተላልፈው መመሪያና ትእዛዝ የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው በድምጽ ብልጫ የሚፈልገውን ውሳኔ አስወስኖ ለመሄድ እቅድ እንዳለው በግልጽ ያሳያል።

ይህ ሁሉ ግርግርና እንቶ ፈንቶ በሕዝብ ላይ የፍርሃት ድባብ ለመጣልና በአስመሳይ እርምጃዎች ዜጎችን ለማማለል ነው። ላለፉት 25 ዓመታት በጭቆናና በብዝበዛ አንጀቱ የተኮማተረው ሕዝብ ግን የወያኔን የማስፈራራትም ሆነ የማስመሰል ቲያትር አልተቀበለም። በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ በትር አልበረገገም፤ በማስመሰል ድራማው አልተታለለም። በሕዝብ የተጠየቁት ጥያቄዎች መሠረታዊና ወሳኝ ስለሆኑ በብልጣብልጥነት በሚደረግ የአስመሳይ ስብሰባ ወይም የሥልጣን ዕድሜን ማራዘሚያ ሽፋን የሆነውን ሹም ሽር ተግባራዊ በማድረግ የሚመለስ አይደለም።

ሕዝብ የጠየቀው የሥርዓት ለውጥ ነው። ጥያቄዎቹ የሚመለሱት ሆነ ችግሮቹ የሚፈቱት ደግም ሕዝብ የሥልጣን ባለቤት ሲሆን ብቻ ነው። የሥርዓት ለውጥ ሳይኖር የአንድ ቡድን፣ የአንድ ዘር፣ የአንድ ፓርቲ የበላይነት፣ ፈላጭ ቆራጭነትና አምባገነንነት አይወገድም። የሥርዓት ለውጥ ከሌለ፤ የሕዝብ ነጻነትና መብት አይከበርም፣ የሕግ የበላይነት አይኖርም። የሥርዓት ለውጥ ከሌለ ሕዝብ በዘርና በቋንቋ እንዲከፋፈል የሚደርስበት ተጽእኖ አይገታም፤ የብሔር ብሔረሰቦች በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት እውን አይሆንም። የሥርዓት ለውጥ ከሌለ የአገር ሀብት ከመመዝበር አይድንም። የሥርዓት ለውጥ እውን ካልሆነ ተጠያቂነት አይረጋገጥም። የሥርዓት ለውጥ ከሌለ ሰላምና መረጋጋት አይገኝም።

ሕዝብ የሚፈልገው ሥርዓተ -መንግሥት፣ ሕዝብ የሥልጣን ምንጭና ባለቤት የሚሆንበት፤ በሕዝብ የሚመረጥና በሕዝብ ቁጥጥር ስር የሚውል ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ነው። በአንድ አገር ውስጥ ሰላምም ሆነ መረጋጋት ብልጽግናም ሆነ እድገት ሊገኝ የሚችለው አገሪቷ በሚገባ የተዋቀሩ የመንግሥት አካሎች፣ ሕጎችና ደንቦች እንዲሁም ተጠያቂነት ያለው የአስተዳደር መዋቅር ሲኖራት ነው። ዴሞክራሲያዊ በሚባሉ የተለያዩ አገሮች የሚገኙት መንግሥታዊ መዋቅሮች የተለያዩ ቅርጽና መልክ ያላቸው በመሆኑ እዚህ ላይ መዘረዘር የሚቻል ባይሆንም በሁሉም ዘንድ ተመሳሳይ የሆነውን መሠረታዊ ይዘት ባጭሩም ቢሆን ማስቀመጡ ለግንዛቤ ይረዳል። አገራችን ህልውናዋን አስከብራ፤ የሕዝቦቿን መብትና ነጻነት አስጠብቃ፤ ሰላምንና መረጋጋትን እውን አድርጋ፣ ለሁሉም ዜጎች የሚዳረስ ብልጽግና አግኝታ ወደ ፊት ልትጓዝ እንድትችል ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉት ዋና ዋና መርሆዎች እውን መሆን አለባቸው፤

- ሁሉም ዜጋ ግልጽ ሆኖለት፤ በግልጽ ተወያይቶበትና ተነጋግሮበት በድምጽ ብልጫ የሚያጸድቀውና ሁሉም ተገዥ የሚሆንለት ሕገ መንግስት
- በማንም ቡድን፣ ፓርቲ፣ ጎሳ፣ የእምነት ተከታይ፣ ...ወዘተ ቁጥጥር ሥር ያልዋሉ ወይም በበላይነት የማይመራቸው ተጠሪነታቸው ለሕገ መንግሥቱ ብቻ የሆነና፤ አንዱ ወገን ከተሰጠው የሥልጣን ገደብ ሲያልፍ ሌላው ሊቆጣጠር በሚችልበት መንገድ የተዋቀሩ መንግሥታዊ አካሎች ማለትም የሕግ አውጭ፤ የሕግ አስፈጻሚና የዳኝነት አካሎች፤

- ከማንም ቡድን ተጽእኖ ነጻ የሆኑ፤ ነጻነት ያላቸው፤ ገለልተኛ የሆኑና ተጠሪነታቸው ለሕገ መንግሥቱ ብቻ የሆነ፤ በሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ የሚዋቀሩ የመከላከያ፣ የጸጥታና የአስተዳደር መዋቅሮች፤
- የሕዝብን ልዩ ልዩ አስተያየትና አመለካከት የሚያስፋፋ፤ እውነቱን የሚያወጣ፤ የተደበቀውን ፈልፍሎ ይፋ በማድረግ የሚያጋልጥ፤ መሪዎችን የሚያርምና የሚወቅስ፤ መልካም አመለካከቶችን የሚያስተጋባና የሚያሰራጭ፤ ነጻነቱና ህልውናው በሕግ የተጠበቀና የተከበረ መገናኛ ብዙሃን፤
- ከማንም ቡድን፣ ፓርቲ፣ የመንግሥት መዋቅር፣ የመከላከያና የጸጥታ ኃይል ጣልቃ ገብነት ነጻ በሆነ መንገድ የሚካሄድ ርቱዓዊና ፍትሃዊ ምርጫ፤

የሚሉት በዋናነት ከሚጠቀሱት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው። ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉ በአገራችን አሉ የሚባል ቢሆንም ለአንድ ቡድን መጠቀሚያ ለይስሙላና ለማስመሰያ የተፈጠሩ በስም ደረጃ ብቻ ያሉ መሆናቸው አከራካሪ አይደለም። ጠባብና ዘረኛ በሆነው በወያኔ ቡድን ታቅደው፤ ህልውና አግኝተውና በቁጥጥር ስር ውለው ላለፉት 25 ዓመታት ድራማ ሲሰራባቸው መቆየታቸው አሌ የሚባል አይደለም። አሌ የሚሉ ካሉ የገዥው ቡድን አባላት ወያም የጥቅም ተከፋይ የሆኑ ብቻ ናቸው። ነገሩን ያልተረዱ ወይም ግር የሚላቸው ካሉ ደግሞ ታሪክን በመረዳትና ዝርዝሩን በደንብ በማጤን እውነታውን መገንዘብ ይቻላል የሚል እምነት አለን። ወያኔ በመሳሪያ ኃይል ሥልጣን ሲይዝ፣ ለይስሙላ ባካሄደው የሕገ-መንግሥት ጉባዔ ለረጅም ጊዜ ሥልጣን ሊያቆየው የሚችለውን የራሱን ፕሮግራም የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት አድርጎ በሥራ ላይ ማዋሉን ማን የሚስተው አለ? የሕግ አውጭው፣ የሕግ አስፈጻሚውና የዳኝነት አካሎች ላለፉት 25 ዓመታት በዚሁ ቡድን ቁጥጥር ስር መቆየታቸውንስ ማን ሊከራከር ይችላል? በመንግሥታዊ አካሎች መካከል የሥልጣን ሚዛን የተጠበቀበትና የአንደኛውን አካል የሥልጣን ገደብ ሌላው አካል የተቆጣጠረበት ሁኔታ ታይቶ ያውቃልን? ቁልፍ ቁልፍ የሆኑ የመንግሥት ሚኒስትር ቦታዎች፤ የመንግስታዊ ተቋሞች የኃላፊነት ቦታዎች፣ ...ወዘተ በወያኔ አባላት ለ25 ዓመታት የተያዙት ለምን ይሆን? በቅርቡ በተከሰተው ሕዝባዊው አመጽ ግፊት አንዳንድ ቁልፍ የሆኑ የሚኒስትር ቦታዎች በሌሎች ተለጣፊ ድርጅቶች አባላት ተተኩ ቢባልም በእነዚሁ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በምክትል ሚኒስትርም ሆነ በሌላ ደረጃ ተሰይመው በመቆጣጠር ላይ ያሉት የማን ድርጅት አባላት ናችው? የመከላከያና የጸጥታ ተቋሞችስ በማን ቁጥጥር ሥር ናቸው? ከመከላከያው ማዕከል ጀምሮ በዋና ዋና ቦታዎች፤ እንዲሁም በክፍለ ጦር፣ በቀጠና፣ በብርጌድ፣ ... ወዘተ በኃላፊነት ቦታ ላይ የተሰየሙት የወያኔ/ሕወሓት አባላት አይደሉምን? የወታደሩ ክፍል የብሔር ተዋጽኦ አለው ቢባልም የወያኔ ቡድንን ሥልጣን ከማንኛውም የታጠቀም ሆነ ያልታጠቀ ኃይል ለመጠበቅ በልዩ መልክ የተደራጀውና የሰለጠነው፤ በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞ የሚያሰሙ ዜጎችን ጭምር በማንኛውም ቦታና ሰዓት ለመግደልና ለመደምሰስ ሙሉ ሙብት የተሰጠውና ለፈጸመው የወንጀል ሥራዎች ተጠያቂ የማይሆነው የአግአዚ ጦር የተሞላው በወያኔ ድርጅት አባላት መሆኑ አገር ያወቀው ጸሐይ የሞቀው ሐቅ ነው። የሰለላውና የጸጥታው ክፍልም ከመሥሪያ ቤቱ ቁንጮ ጀምሮ እስከክፍል ኃላፊዎች ድረስ የተያዘው በዚሁ ድርጅት አባላት ሲሆን በዚሁ መሥሪያ ቤት ሥር ያሉ እንደኢሚግሬሽን ዓይነት የተለዩ ክፍሎች ደግሞ ቦታቸው ሙሉ በሙሉ ወይም ዘጠና ከሙቶው የተያዘው ከአንድ ጎሳ በመጡ የወያኔ አባላት ነው። በወያኔ ባለሥልጣኖች ሙብታቸውን የተጠቀሙ ዜጎች በሚገደሉበት፤ በሚታሰሩበትና ታስረው በሚሰቃዩበት እንዲሁም ትክክለኛ ፍርድ በተነፈጉበት ሁኔታ በአገሪቱ ውስጥ የሕግ የበላይነትና ፍትህ አለ ማለት አይቻልም። በኤፈርት ሆነ በማቴክ፤ በምርት ገበያ ሆነ በሌላ የንግድ ድርጅት ስም ሥልጣንን የተቆጣጠሩ የወያኔ አባላት በብዙ ቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር የአገሪቱን ሀብት የሚዘርፉበትና ወደ ውጭ የሚያወጡበትም የውንብድና ተግባርም ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት ነው። እንዲህ እያልን

በመቀጠል የወያኔን አገዛዝ ምንነት ማሳየት ይቻላል። ዝርዝሩ ብዙ ስለሆነ ሁሉንም እዚህ መጥቀሱ አስቸጋሪ ቢሆንም ከላይ የተጠቀሱት በመጠኑም ቢሆን የአገዛዙን ውስጣዊ ገጽታ ይገልጻል ብለን እንገምታለን።

በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ሕዝባችን እየሞተ፣ እየቆሰለ፣ እየታሰረና እየተሰቃየ እንዲሁም ንብረቱ እየወደመና እየተዘረፈ ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ ለሆነ ጊዜ አመጹን ያካሄደውና ያቀጣጠለው ከላይ የተጠቀሰውን አስከፊውን የአንድ ቡድን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ አስወግዶ በምትኩ ሕዝብ የሥልጣን ምንጭ የሆነበት፤ መብት የሚጠበቅበትና የሚከበርበት፤ እኩልነት የሚረጋገጥበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለመመሥረትና ለመገንባት ነው። ስለሆነም ዜጎች ደም የከፈሉበት፤ የተሰቃዩበትና አካለ ስንኩላን የሆኑበት ሕዝባዊ ጥያቄ በማናቸውም ዓይነት "ሹም ሽር"፤ "በጥልቀት መታደስም" ሆነ በይስሙላ ውይይት የሚመለስ አይሆንም። በአሁኑ ወቅት አመጹ የቀዘቀዘ ቢመስልም፤ የተዳፈነ እንጅ ያልጠፋ፤ ያንቀላፋ እንጅ ያልሞተ መሆኑ ግልጽ ነው። በገሀድ የሚታየውና ያልተደበቀው የኢትዮጵያ የሕዝብ ብሶትና ቁጭት የሚያሳየን፤ የተዳፈነው አመጽ በአዲስ ንፋስ ተንቀልቅሎና ነባልባሉ ከአድማስ አድማስ ተሰራጭቶ ይህን አስከፊ አገዛዝ ከመሠረቱ ገርስሶ ሊጥል የሚችል መሆኑን ነው።

የአሁኑ ትውልድ እያካሄደ ያለው የአመጽ እንቅስቃሴ ከየካቲት 66-ኡ ሕዝባዊ አመጽና ከአመጹ በኋላ ከተከተሉት ሁኔታዎች የተማረውም የሚማረውም ትምህርት ይኖራል። በየካቲት 66-ኡ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሁሉም ዜጋ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጾታና በእድሜ፣ በመኖሪያ ቦታ፣ በሙያ፣ በሥራ መስክ፣ በትምህርት ደረጃ፣ ... ወዘተ ሳይለያይ ክንዱን በማስተባበር ታግሎ የንጉሡን አገዛዝ ገርስሷል። ካለፈው አንድ ዓመት ተኩል ጀምሮ በተለያዩ አካባቢዎች ሲካሄዱ የነበሩት ሕዝባዊ አመጾች የወያኔ አገዛዝ የጫነውን የዘር ልዩነትን በመስበርና አንዱ ክፍል ያነሳውን የትግል ጥያቄ ሌላው ወገን በመደገፍ የጋራ የሆነውን ሕዝባዊ ትግልና ጥያቄ ለማጠናከር መሞከራቸው ከየካቲት 66-ኡ እንቅስቃሴ የወሰዱት ትምህርት እንዳለ የሚያስገነዝብ ቢሆንም የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማቀፍና የትግሉንና የአመጹን አድማስ ወደተለያዩ አካባቢዎች በማስፋት በኩል እንቅስቃሴዎቹ የሚቀራቸው ሥራ እንደነበር መረዳት ይቻላል። የየካቲት 66-ኡ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የአጼውን አገዛዝ መገርሰስ ቢችልም በወቅቱ የተደራጁትና የእንቅስቃሴው አካል የነበሩ ክፍሎች ያልተጠናከሩና ለጋ ስለነበሩ ሕዝባዊ መንግሥት የሚለው የእንቅስቃሴው ዓላማና መዳረሻ በወቅቱ በሚገባ በተደራጀውና ኃይልን ባከማቸው በምርጥ መኮንኖች ቡድን ተጠልፎ ግቡን ሳይመታ ቀርቷል። ለግል ሳይሆን ለሕዝባዊ ጥቅም፤ ለዝና ሳይሆን ለሕዝብ መብትና ነጻነት ራሳቸውን መስዋዕት ለማድረግ የቆረጡ ዜጎች እስካሉ ድረስ የወቅቱ ሕዝባዊ አመጽ አገዛዙን ማስወገድ መቻሉ የማያጠራጥር ቢሆንም በጥልቀት ተሃድሶ ባገኘው ወያኔ ቁጥር 2 ወይም በሌላ የተደራጀ ኃይል እንዳይጠለፍ፤ የሕዝብ ወገኖች የሆኑ ሁሉ በህቡዕና በሌላ አመች በሆነው መልክ የበለጠ መደራጀታቸውና ክንዳቸውን አስተባብረው መታገል፤ አማራጭ የሌለው መንገድ ነው እንላለን። ከሕዝባዊ ትግል ውጭ ለአፍታም ተለይቶ የማያውቀው ኢሕአፓ ሕዝባዊ አመጹን ለማጠናከር የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ መሆኑን እየገለጸ ትግሉ አስከፊውን አገዛዝ አስወግዶ ሥልጣን የሕዝብ ምንጭ የሆነበት ሥርዓት እውን እስኪሆን ድረስ ኃይላችንን አስተባብረን እንታገል በሚል ጥሪውን ያስተላልፋል።

አስከፊው አገዛዝ በሕዝባዊ አመጽ ይወገዳል!!
የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን ጠብቆ በሚያካሄደው ትግል ድልን ይጎናጸፋል!!